# የማህበረሰብ ደህንነት ጥበቃ ላይ ያለ እምነት (Community Trust protections) በሞንትጎመሪ ካዉንቲ ውስጥ በአሁን ጊዜ ህግ ሆነዋል።

## ይህ ለእርስዎ ምን ማለት ነው:-

### የእርስዎ ደህንነት ቅድሚያ ይሰጠዋል

- ስለ የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታዎ (immigration status) ሳይጠየቁ ወንጀሎችን ለፖሊስ ደውለው ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።
- የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶችን ያለ ፍርሃት መጠየቅ ይችላሉ።
- የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታዎ (immigration status) ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ ሳይኖረው ከአካባቢው ፖሊስ ጋር መተባበር ይችላሉ።

### የኢሚግሬሽን ህግን በማስፈጸም ዙሪያ ያሉ ግልጽ ገደቦች

- የካውንቲው አገልግሎቶች የሲቪል ኢሚግሬሽን ህግን ለማስፈጸም(civil immigration enforcement) ስራ ላይ አይውሉም።
- የካውንቲው ሰራተኞች የፌደራል ኢሚግሬሽን ህግን ለማስፈጸም(federal immigration enforcement) ሃላፊነት የለባቸውም።

### የካውንቲው አገልግሎቶች እኩል ተደራሽነት

- የካውንቲው አገልግሎቶች የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታ (immigration status) ግምት ውስጥ ሳይገባ ለሁሉም አገልግሎት ይሰጣሉ።
- የካውንቲው ሰራተኞች የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታን (immigration status) መሰረት በማድረግ ማስፈራራት ወይም ማሸማቀቅ አይችሉም።
- የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታዎን (immigration status) በተመለከተ (በህግ ካልተጠየቀ በስተቀር) አይጠየቁም።
- ካውንቲው የተለያዩ የመታወቂያ ዓይነቶችን ይቀበላል (የውጭ ፓስፖርቶችን ጨምሮ)።

### የእርስዎ የግል መረጃ ደህንነት የተጠበቀ ነው

- የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታዎን (immigration status) በተመለከት ያሉ አላስፈላጊ ጥያቄዎችን ከካውንቲው ፎርሞች ውስጥ እንዲወጡ ያደርጋል።
- ሚስጥራዊ የግል መረጃዎች በጥንቃቄ ይያዛሉ።
- የኢሚግሬሽን ሰራተኞች በዳኛ የተፈረመ የመግቢያ ፈቃድ (warrant) ሳይኖራቸው ለህዝብ ክፍት ወደሆኑ የካውንቲው ሕንጻዎች መግባት አይችሉም።
- የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት በካውንቲው የእስረኛ ማቆያ ተቋማት ውስጥ ያሉ እስረኞችን በተመለከት መረጃ ሲጠይቁ እስረኞቹ በ 48 ሰዓታት ውስጥ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

## ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ፡-

የፌዴራል ህጎችን ማስፈጸም የፌደራል መንግስት ሃላፊነት ነው እንጂ የሞንትጎመሪ ካዉንቲ መንግስት አይደለም። የእኛ ትኩረት በአካባቢው በሚሰጡ አገልግሎቶች እና በህዝብ ደህንነት ላይ ነው። ይህ ግልጽ የሆነ የተግባር ልዩነት ሁሉም ነዋሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ወንጀሎችን ሪፖርት ማድረግ እንዲችሉ፣ ከፖሊስ ጋር በቀላሉ እንዲግባቡ እና በአካባቢው ከሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንደሚረዳቸው ተስፋ እናደርጋለን። በካውንቲያችን ውስጥ ከፌዴራል ኦፊሰሮች ጋር የሚከሰት ጉዳይን በተመለከተ ፣ ጉዳዩ በሜሪላንድ የወንጀል ሕግ መሠረት በጥልቀት መመርመሩን ለማረጋገጥ ተገቢውን ምርመራ ከሚያደርጉ የስራ አጋሮች ጋር በትብብር እንሰራለን።

ይህ መረጃ በሞንትጎመሪ ካዉንቲ ውስጥ የማህበረሰብን እምነት በማጠናከር ረገድ የስደተኞች ጥበቃ ህግ (Immigrant Protections Act ) ስር ያሉትን ቁልፍ ጥበቃዎችን ያብራራል። እነዚህ ጥበቃዎች የካውንቲውን ህግ መሰረት ያደረጉ ናቸው። ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው በፌብሯሪ 2026 ነው።

# የማህበረሰብ መረጃ እና የድጋፍ አገልግሎቶች

የሚከተሉት ድርጅቶች እንደ ማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ተዘርዝረዋል። እነዚህን ድርጅቶች መዘርዘር ሞንትጎመሪ ካውንቲ ድርጅቶቹን እንደሚደግፍ ወይም እንደሚያጸድቅ አያሳይም።

| ድርጅት/ አገልግሎቶች | መገኛ አድራሻ/ኪውአር(QR) ኮድ |
|---|---|
| ጊልክሪስት (Gilchrist) የስደተኛ የመረጃ እና የአገልግሎት ማዕከል<br>ነጻ፣ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚሰጥ አገልግሎት እና አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል ፤ይህም መብትዎን ይወቁ የሚለውን ጨምሮ፣ትምህርቶችን እና የህግ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ዝርዝር ያካትታል | 240-777-4940 |
| የቤተሰብ ዝግጁነት መመሪያ<br>ከዩናይትድ ዊ ድሪም (United We Dream)<br>ቀጥታ ሊንክ (እንግሊዝኛ እና ስፓኒሽ) | |
| የሞንትጎመሪ ካዉንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች<br>የስደተኛ (immigrant) ድጋፍ አገልግሎት<br>ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች | |
| የምግብ ድጋፍ አገልግሎቶች<br>በሞንትጎመሪ ካዉንቲ ውስጥ የምግብ ድጋፍ አገልግሎቶች መመሪያ፣ ይህም ምግብ የመኖሪያ ቤት ድረስ የሚያመጡ የምግብ አቅራቢዎች ዝርዝርን ያካትታል። | |
| እኛ ካሳ ነን (We Are CASA)<br>ፈጣን ምላሽ ሰጪ የስልክ መስመር<br>(Rapid Response Hotline)<br>ማንኛውንም ከአይስ (ICE) ጋር የሚከሰቱ ግንኙነቶችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል ፈጣን የጥቆማ ስልክ መስመር። | 1-888-214-6016 |
| አይደንቲቲ (Identity)<br>ከቤተሰብ ዝግጁነት ጋር የተያያዘ እገዛ | |

MONTGOMERY COUNTY · 1776 · GARDEZ BIEN · MARYLAND